በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

የካቲት 30 ቀን 2011
አዲስ አበባ
መግለጫ

## በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት እና በአዲስ አበባ ከተማ መካከል ያለዉን የአስተዳደር ወሰን ዉዝግብ በተመለከተ

በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር መካከል ያለዉ የአስተዳደር ወሰን በአግባቡ አለመካለሉ ይታወቃል፡፡ ይህን ችግር በዘላቂነት በመፍታት የአስተዳደር ወሰን አካባቢዎች የግጭት እና የንትርክ አጀንዳ ከመሆን ይልቅ የልማት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የሚረጋገጥባቸዉ አካባቢዎች እንዲሆኑ በማሰብ ችግሩን ጥናት ላይ የተመሰረተ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት ከኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት እና ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የተዉጣጣ የጋራ ኮሚቴ ተዋቅሮ ጥናቶች ቢደረጉም የጥናቱ ዉጤት ላይ ተመስርቶ ጉዳዩን መቋጨት ባለመቻሉ በኦሮሚያ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ መካከል ያለዉ የአስተዳደር ወሰን ጉዳይ አወዛጋቢ ሆኖ ቀጥሏል፡፡

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት እና በአዲስ አበባ አስተዳደር መካከል ዕልባት ያላገኘ የአስተዳደር ወሰን ይገባኛል ጥያቄ መፍትሄ ሳይሰጠው የጋራ መኖሪያ ቤቶች እጣ መዉጣቱ ዉዝግብ አስነስቷል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ እና በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መካካል ያለዉን የአስተዳደር ወሰን ጥያቄን በዘላቂነት ለመፍታት ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናቶችን መሰረት በማድረግ እና ህዝቡን በማሳተፍ ዘላቂ መፍትሄ ማስቀመጥ ወሳኝ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ በዚህም መሰረት ስምንት አባላት ያሉት ከፌዴራል መንግስት፣ ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት እና ከአዲስ አበባ መስተዳድር የተዉጣጡ አባላት ያሉት ኮሚቴ ተዋቅሮ ለጉዳዩ መፍትሄ የሚሆን ምክረ ሀሳብ እንዲያቀርቡ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ የኮሚቴዉ አባላት የሚከተሉት ናቸዉ:-

1. ወ/ሮ ሙፈሪያት ካሚል ፣ የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር (ሰብሳቢ)
2. ወ/ሮ ጠይባ ሀሰን (አባል)፣ የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክትል ፕረዝዳንት
3. አቶ አህመድ ቱሳ (አባል)፣ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በምክትል ፕረዝዳንት ማዕረግ የከተማ ልማት ክላስተር አስተባባሪ
4. ዶ/ር ግርማ አመንቴ፣ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በምክትል ፕረዝዳንት ማዕረግ የገጠር ልማት ክላስተር አስተባባሪ (አባል)

5. አቶ ታከለ ዑማ ፣ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ምክትል ከንቲባ (አባል)
6. አቶ እንዳወቅ አብጤ ፣ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የማህበራዊ ክላስተር አስተባባሪ (አባል)
7. ዶ/ር ሰለሞን ኪዳኔ ፣ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በምክትል ከንቲባ ማእረግ የኢኮኖሚ ክላስተር አስተባባሪ (አባል)
8. አቶ ተስፋዬ ቤልጅጌ ፣ የአዲስ አበባ ከተማ የከንቲባዉ የህዝብ አደረጃጀት አማካሪ (አባል)

//